Jan 18,2014

# ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ

ጌታን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ከመቀበሌና ሜ አድርጌ ከመሾሜ በፊት ህይወቴ እንደ አይን የጠፉና የተበላሸ ነበር፡፡ሀይለኛ የሱስ ቀንበር እላዬ ላይ ነበርና የየቀኑ ኑሮዬ የስቃይና የመከራ ነበር፡፡ማጠጣት ነበረብኝ፤መቃም ነበረብኝ፤ሜጩ ነበረብኝ፡፡ከዚህም የተነሳ ማህበራዊ ህይወቴ በጣም የተበላሸ ነበር፡፡

ከሱሱ በስተጀርባ የከፉ ተጽእኖ እንደ ነበር በሕይወቴ ቅንጣት አልጠራጠርም፡፡አሁን ላይ ቆሜ ሳየው ባሁኑ ሰአት መኖሬ እራሱ ተአምር ነው፡፡ሞቴ ይፈጥናል የሚል ግምት በኔም በአቅራቢያ ባሉ ሰዎች ሁሉ የሚታሰብ ጉዳይ ነበር፡፡እንደዚህ አይነቱ ህይወት ከ 15 አመት በላይ አሸኝ፡፡ከዚህ ስቃይ ገፍትሬ ለመውጣት ብሞክርም <<ታጥቦ ጭቃ>> አይነት ኑሮ ለረጅም ዘመን ገፋሁ፡፡ውስጤ ስቃይ ነበር፤ለቅሶ ነበር፤ሀዘን ነበር፤ተስፋ መቁረጥ ነበር፤ሞትን በሀይል መመኘት ሁሉ ነበር፡፡

እያንዳንዱን ቀን በማጠጥ ለማስወር የማጠጥ ባሪያ ብሆንም እንዳወም የነበሩብኝ ወስብስብ ችግሮች እየገጠጡ ማጡ፡፡ችግሮቹን የሚያባብሱ ሰዎች ነበሩ፤እኔም አባብሰው ነበር፤የነበርኩበት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ያባብሱት ነበር፡፡ስለዚህ በአጭር ቃል ረግረግ ጭቃ ወስጥ (መዝ 40፡2) ነበርሁ ማለት ይቻላል፡፡

የዘወትር የወስጥ ስቃዬና ጩኸቴ <<ማን ያወጣኛል?>> የሚል ነበር፡፡ወደ ቤ/ክ አልፎ አልፎ ሄጄ ከነበርኩበት ጉድ ለመውጣት ብሞክርም ወስጤ በሚገባ ስላልተለወጠ ታይታዊ የሆኑ ጊዜያዊ ለወጦች ስለ ነበሩ አንድ መጥፎ ክስተት ሲገጥመኝ የነበረኝ የሱስ ቀንበር እጥፍ ድርብ ያገረሸ ነበር፡፡

ከላይ በጠቀስኳቸው ወስብስብ ሁኔታዎች ሁሉ ነገሬ ተበላሽቶ በቃልኝ ከዚህ በኃላ ሰው አልሆንም፤ዳግመኛ አልነሳም ፤ብሩህ ቀናትን አላይም ብዬ ደመደምኩ፡፡ዘመድ፣ወዳጅና ቤተሰብ ሁሉ ራቀኝ፡፡መዝ 31፡2 ላይ <<እንደ ሞተ ሰው ከልብ ተረሳሁ፤እንደ ተበላሸ እቃም ሆንሁ>> የሚለው የመዝሙረኛው ዳዊት አገላለጽ በሚገባ የነበርኩበትን ማጥ የሚገልጸው ይመስለኛል፡፡በሰው ሁሉ ዘንድም ተረሳሁ፡፡

በእንደዚህ ወስብስብ ታሪክ ወስጥ እያለፍኩም ቢሆን የእግዚአብሔር ቃል በወስጤ ያለ ሟቁረጥ ይዘራ ነበር፡፡ይህ ዘር በቅሎም ፍሬ ማፍሪያው በጌታ ጊዜ ደረሰ፡፡እናም ተስፋዬ ተሟጦ ወሀ የሚያጠጣኝ ዘመድ ወገን መሉ በመሉ ሳጣ ወደ አምላኬ መሉ በመሉ የመመለስ ጉዳይ በአንድ ድንቅዬ ቀን የዛሬ 15 አመት በግማሽ ቀን ገፍቶ አየለ፡፡በዚህ ወስጣዊ ትንቅንቅ እኔነቴ ለሁለት ተከፍሎ ትግል ሆነ፡፡ይሉኝታ፣የሰው ፍርሀት፣የሱስ ተጽእኖው

እስራት፣የብቸኝነቱ መከራ ሁሉ እንደ ዛፍ እያወዛወዘኝ በሌላ በኩል ወደ እርሱ ብመለስ የማገኘውን እረፍት እያሰብኩ ለ 6 ሰአታት ያህል የታገልሁት ትግል በሕይወቴ አይረሳኝም፡፡

ወደ ልቤም ተመልሼ(ሉቃ 15:17) ስወስንና ከነገ ጀምሮ ወደ አባቴ ቤት እሄዳለሁ፤አለምን እክዳለሁ፤ሰይጣንንና አገዛዙን እክዳለሁ፤የስጋን መንገድ አልከተልም፤እስከ መጨረሻ የእርሱ ባሪያ እሆናለሁ ብዬ በልቤ ልክ ቃል ኪዳን ስገባ፡-

- ቤቱ በብርሀን ተሞላ
- የደስታ መንፈስ በውስጤ ፈሰሰ
- ልዩ የሆነ የሰላም መንፈስ አጥለቀለቀኝ
- ከጨለማ ወደ ብርሀን እንደ ተሸጋገርሁ ታወቀኝ(ቆላ 1፡14)

ከዚያ ድንቅ ውሳኔ በኃላ  የጫት፣የሲጋራ እና የመጠጥ ሱስና ቀንበር ባንድ ቀን ሙሉ በሙሉ ተሰበሩ፡፡የሚገርመው ነገር እነዚህን ሱሶች ባቆምኩ የመጀመሪያዎቹ ቀናትና ሳምንት ውስጥ እራስ ምታት እንኳን አልነበረኝም፡፡ይሄ ሁኔታ ሁልጊዜ ይገርመኛል፡፡ከዛ ሁሉ ቀንበር ተላልቄ የነጻነት አየር እየተነፈስሁ እነሆ አሁን 15 አመት አልፎኛል፡፡ኢሳ 61፡1-3 እንደሚል ፡-

- ብዙ የልብ ስብራት ነበረኝ ተጠግኛለሁ
- ምርኮኛ ነበርሁ ነጻ ሆኛለሁ
- ታስሬ ነበር ተፈትቻለሁ
- አለቅስ ነበር የደስታ መንፈስ በማያቋርጥ ሁኔታ በውስጤ ፈሷል
- በአመድ  ፋንታ አክሊል በሀዘን ፋንታ የምስጋና መጎናጸፊያ ተደርቦልኛል
- የጉዳቴ መጠን ትንሽ አልነበረም የካሳዬ ብዛትም ከአእምሮ በላይ ሆኗል

ይህ የፍቅር አምላክ ብዙ ድንቅ ነገሮችን አሳየኝ ፡፡ህይወቴን በመንፈሱ ዘይት አለማለመው(መዝ 92፡10)፡፡

ስለዚህም እንዲህ ብዬ አንድ ህይወቴን በሚገባ በመግለጹ የምወደው መዝሙር አለና እንዲህ ብዬ አዜማለሁ፡ -

አየሁ ጌታዬ ከንዱን አንስቶ

የጠላቴን ራስ ሲቀጠቅጠው

እስራቴንም ሲበጣጥሰው

ሞት ሞት የሸተተውን ህይወት

በአዲስ መአዛ ሲለውጠው!!

እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁና ምስክርነቴን ልቋጭ –

ለመሆኑ እርሱን የሚመስል ፈዋሽ፤አለምሌም አደሶና አበርትቶ የሚያቆም ከወዴት ይገኛል?የተጣለንስ የሚያነሳ ማን ነው?

ለኔ መልሱ ፡–የለም ነው!!

በእንደዚህ አይነት የውስጥ ባዶነትና እርካታ የለሽ ህይወት ውስጥ ያላችሁና ሰላም የሌላችሁ ይህንን ነው የምላችሁ፡፡ወደ እርሱ በትህትና ብትመለሱ ይገላግላችኋል፡፡በደስታ ማንፈስም ይባርካችኋል፡፡ይሉኝታን ሰብራችሁ ወደ እርሱ ኑ!

እርሱ ብቻውን ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን !!!!!!

ይህንን ምስክርነት በቅርብ ጊዜ በመጽሀፍ መልክ ላወጣው በቂ ዝግጅት እያደረግሁ ነውና ሙሉውን ታሪኬን ታነቡታላችሁ፡፡ተባረኩ!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

beke_abay@yahoo.com

240-330-5004